# ቀስተደመና ሬድዮ ትችት

( ሰኔ 6 ቀን 1994 እ.ም.)

June 13, 2002

## የምግብ ሉአላዊነት ሲባል............

በያዝነው ሳምንት በሮማ ከተማ ተቀምጦ የነበረውና ምንም ውጤት ሳያስመዘግብ የተበተነው
«የአለም የምግብ ጉባኤ» በርሃብ ጉዳይ ለመምከር የተጠራ የመጀመሪያ ጉባኤ አልነበረም። በ
አለም ደረጃ ርሃብን የማጥፋት ጉዳይ ሲወራለትና ሲዛትበት ቢያንስ አርባ አመት ሆኖታል። በ
1955 እ.ም. በዋሽንግተን ከተማ የመጀመሪያው «የአለም የምግብ ጉባኤ» ሲደረግ ሟቹ ፕሬዜዳ
ንት ኬነዲ ባደረጉት ንግግር « በኛ ትውልድ ዘመን ርሃብን ከምድር ገጽ ጨርሶ ለማጥፋት ች
ሎታውም አለን አቅሙም አለን። የሚያስፈልገን የፖለቲካ ቁርጠኝነት ብቻ ነው» በማለት ለአ
ለም መሪዎች ጥሪ አስተላልፈው እንደነበረ ይታወሳል። ይህ ከተባለ ከአስር አመት በኋላ ደግ
ሞ የርሃብ ነገር እየሰፋና እየጠና እንጂ ምንም መሻሻል ስላላሳየ ሌላ «የአለም ምግብ ኮንፈራን
ስ» በሚል ሌላ የመሪዎች ስብሰባ ተጠራ። እዚህ ላይ በተላለፈው ውሳኔ እንዲያውም ለርሃብ
መውደም ቀን ቀጠሮ ተሰጠ። በግልጽ የተቀመጠው አላማ ርሃብን በአስር አመት ውስጥ ከምድ
ር ገጽ የማጥፋት ግብ ነበር። የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሃንሪ ኪሲንጀር በዚ
ህ ስብሰባ ባደረጉት በጊዜው ብዙ ባነጋገረ ንግግራቸው « ከዚህ እስከ አስር አመት ድረስ ማን
ም ልጅ የትም ይሁን የት ጦሙን አለማደሩን ማረጋገጥ ይኖርብናል» ሲሉ ተደምጠው እንደነበ
ረ ይታወሳል። ይህም አልሰራም። ርሃብ እየጠናና እየሰፋ ቀጠለ።

በ1989 እ.ም. እንደገና «የአለም መሪዎች የምግብ ጉባኤ» ተብሎ ሌላ ስብሰባ ተጠራ። በመ
ሃል በዚች በምግብ በተትረፈረፈች አለም የህዝቦች መራብ ነገር በድርቅና በሌላ የተፈጥሮ አ
ደጋ ብቻ ሊሳበብ እንደማይችል፣ችግሩንም ለመወጣት የበለጸጉት አገሮች ከጎተራቸው እየቆነጠ
ሩ በሚለግሱት የምግብ እርዳታ ብቻ የትም እንደማይደረስ ብዙ ግንዛቤ ተገኘ። ከዚህ አልፎ
ተርፎም የርሃብ ችግር በሚራቡ አገሮች ባለው ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በአለም ከበለጸጉት አ
ገሮች የእርሻ ሁኔታ፣ ከእርዳታው አሰጣጥ ዘዴና ከአለም የንግድ አሰራር ጋር የተቆራኘ መሆኑ
ግልጽ እየሆነ መጣ። ችግሩ በአመት በመቶ ቢልየኖች የሚቆጠር ዶላር ጥቅም የሚነካ ውስብስ
ብ ችግር እንደሆነ ሰፊ ግንዛቤ ተገኘ። በእርግጥ ርሃብን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ከተፈለገ በአ
ለም የንግድ አሰራርና በእርዳታው አሰጣጥ ዘዴ መሰረታዊና የበለጸጉ አገሮችን የኢኮኖሚና የፖ
ለቲካ ጥቅም የሚጠናወቱ ለውጦች እንደሚያስፈልጉ ግልጽ እየሆነ መጣ። ይህ አይነቱ ለውጥ
ደግሞ እንዲሁ በቀላሉ ሊከናወን እንደማይቻል የዚያኑ ያህል ግልጽ ሆነ።

ይህ ግንዛቤ በሰፈነበት ሁኔታ በርሃብ ጉዳይ ለመነጋገር እንደገና በ1989 እ.ም. የተጠራው የ
መቶ ሰማንያ አምስት አገሮች መሪዎች የተሳተፉበት «የአለም የምግብ ጉባኤ» ቀደም ባሉት ጉ
ባኤዎች የታዩት «ቁርጠኛ» ዛቻዎች አልተንጸባረቁበትም። ከምድር ገጽ ርሃብን ስለማውደም
አያወራም። እንደግብ ተደርጎ የተወሰደው ባለም በርሃብ ከሚጠቁ ስምንት መቶ ሚልዮን ዜጎች
በሃያ አመት ጊዜ ገደብ ውስጥ ማለትም እስከ 2008 (ወይም እ.እ.አ. 2015) ድረስ አራት መቶ
ሚልዮኑ ጠግበው የሚያድሩበት ሁኔታ መፍጠር ነበር። ።

አስፈላጊዎቹ ለውጦች ከተደረጉ ህዝቦች ራሳቸው ችግሮቻቸውን ፈተው ርሃብን ሊያወድ
ሙ ይችላሉ የሚሉ ወገኖች በወቅቱ ይህንን «የርሃብተኛን ቁጥር በሃያ አመት በግማሽ መቀነስ
» የሚል ግብ በጥብቅ ተቃወሙት። በዚች በምግብ በተትረፈረፈች አለም ግማሻችሁ እስከዛሬ
ሃያ አመት ድረስ ምግብ ይሰጣችኋል ግማሻችሁ ደግሞ ገና መጠበቅ ይኖርባችኋል የሚለውን
አካሄድ በስፍራው ከተገኙት የአለም መሪዎች መሃከል የኩባው ፊዴል ካስትሮ በመዝጊያ ንግግ
ራቸው ላይ «አሳፋሪ ውሳኔ ነው» በማለት አወገዙት።

ይህ የሰሞኑ የሮማ የአለም ምግብ ጉባኤ የቀደመው ስብሰባ ውሳኔ «የት እንደደረሰ» ለመገ
ምገም የተጠራ ጉባኤ ነበር። ከመሪዎቹ ተለይተው በዚያው በሮማ ከተማ፣ በዚሁ በርሃብ ጉዳ

ይ የተሰበሰቡ የስድስት መቶ የአፍሪካና የበለጸጉት አገሮች የሲቪክ ስብስቦች አንዱ የሆነው « ፉድ ፈርስት» ወይም «ቅድሚያ ለምግብ» የተባለው ድርጅት በስፍራው ባሰራጨው መግለጫ ሁኔታውን በአጭሩ ሲያቀርበው « የዛሬ አምስት አመት ይህንን ውሳኔ ፊዴል ካስትሮ አሳፋሪ ብለው ጠርተውት ነበር። ከዚያ ወዲህ የሆነውንና የሚሆነውን ስናይ ነገሩ ከአሳፋሪም አሳፋሪ ሆኖ ተገኝቷል» በማለት በነዚህ ስብስቦች አካባቢ ያለውን ምሬት አንጸባርቋል።

ለመሆኑ ይህ ይህ በሃያ አመት ርሃብን በግማሽ እንቀንሳለን የተባለው ዛቻ ምን ደረሰ? የትም ደረሰ ማለት አይቻልም። «አሳፋሪ» የተባለው ውሳኔው ግቡን ይመታ የነበረው በአለም የርሃብ ተኛው ቁጥር በአመት በሃያ ሁለት ሚልዮን ቢቀንስ ነበር። በየአመቱ እየቀነሰ የመጣው በስድስ ት ሚልዮን ብቻ ነው። አንዳንድ አካባቢዎች ርሃብ የባሰውን ተስፋፍቷል። በዚህ አያያዝ አን ዳንድ የሲቪክ ስብስቦቹ ተወካዮች እዚህ ግብ ለመድረስ ምናልባት 2035ን መጠበቅ ያስፈልጋል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ገና 2050ን መጠበቅ ያስፈልጋል የሚል ግምት ሰጥተዋል። የተመድ የምግ ብና የእርሻ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ጃክ ድዩፍ ደግሞ እንዳያያዛችን ከሆነ እዚህ ግብ ለመድ ረስ እስከ 2060 እ.ም. መጠበቅ ይኖርብናል ሲሉ ተደምጠዋል።

ይህ እንግዲህ እስከዛሬ ስልሳ አመት ድረስ ርሃብ፣ ድርቅ፣ የአካባቢ ብክለትና እነዚህ ሁሉ እያስከተሉ ያሉት ይህ ነው የማይባል የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ እየተጋገዙ የሚፈታተኗቸው ርሃብተኞች ህዝቦቻችን በግማሽ ይቀንሳል ከተባለለት ርሃብ ቀድመው ካልጠፉ ማለት ነው።

መፍትሄው ምንድን ነው? የበለጸጉትን አገሮች «ጎተራዎቻችሁ ሞልተው ተትረፍርፈዋልና ተ ርበናል አካፍሉን!» ማለቱ የትም አያስኬድም። በዚች በምግብ ምርት በተትረፈረፈች አለም ሰ ዎች መራባቸው ልክ አይደለም እያሉ ደረት መምታትም መፍትሄ አይደለም። ርሃብን የመቋቋ ምና የማውደም ትግል እጅግ ውስብስብ ቢሆንም ዛሬ በአሜሪካም፣ በአውሮፓም፣ በአፍሪካም፣ በእስያም እየተነሳሳ ያለው የህዝቦችና በተለይ የሲቪክ ማህበራት እንቅስቃሴ ርሃብን «የመቀነስ » ሳይሆን ከዚች ምድር ገጽ ጨርሶ የማውደም አላማና ለዚህም ተጨባጭ መፍትሄ ይዞ የሚን ቀሳቀስ ሃይል ነው።

ከሶስት አመታት ወዲህ ከሲያትል እስከ ጀኖዋ፣ ከፖርቶ አሌግሬ እስከ አፍሪካ ሶሻል ፎረ ም የህዝቦችን መብት ጥያቄ እያነሱ የሚንቀሳቀሱት ሃይሎች ለዚህ ጸረ ርሃብ ግብ ከሚያቀርቡ ዋቸው መፍትሄዎች ዋና ዋና የሚባሉትን ሁለቱን በአጭሩ እንጥቀስ። የመጀመሪያው በአለም የ ሰፈነውን የንግድ አሰራር በመቃወም እነዚህ የለውጥ ሃይሎች «ፍትሃዊ ንግድ» ወይም «ፌር ትሬድ» ብለው የሚታገሉለት መፍትሄ ነው። ሁለተኛው ደግሞ «የምግብ ሉአላዊነት» (ፉድ ሶ ቨረኒቲ) ወይም ህዝቦች ራሳቸውን የመመገብ ሉአላዊ መብት የሚለው የትግል ጥሪ ነው። ሁሌ ሽም ለኛ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉትን ያህል በቀጥታ የበለጸጉትን አገሮች መሰረታዊ የኢኮኖሚ ና የፖለቲካ ጥቅሞች የሚነኩ ስለሆኑ በደቡብም በሰሜንም አገሮች ያሉ የለውጥ ሃይሎች ተባ ብረው ካልታገሉላቸው ግባቸውን አይመቱም።

«ፌር ትሬድ» ወይም ፍትሃዊ ንግድ መነሻ ነጥቡ አሁን በአለም ደረጃ በነጻ ገበያ መርህዎ ች መሰረት ይካሄዳል የሚባለው የንግድ ሂደት ፍትሃዊ አይደለም የሚል ነው። ለበለጸጉት አገ ሮችም ለኛም እኩል አይሰራም። ለምሳሌ የደቡብ አገሮችን የእርሻ ምርቶች እንውሰድ። ከበለ ጸጉት አገሮች ገበያ ጋር ሲነጻጸሩ የኛ በጣም ርካሽ ናቸው። በነጻ ገበያ የመገበያየት መርህዎች መሰረት እነዚህ ምርቶች የበለጸጉት አገሮች ገበያ እንዳይደርሱ በከፍተኛ የታሪፍ አጥርና በሌ ሎች ሌሎች ሰበቦች ይታገዳሉ። ነገር ግን ምእራባውያን በዚህ አሰራራቸው የሚሉት «አትድረ ሱብን፣ አንደርስባችሁም» አይደለም። ድሃ አገሮች ለአምራቾቻቸው የታሪፍ ጥበቃ እንዳያደር ጉ አስገድደው አሁንም ከነጻ ገበያ መርህዎች ውጭ በመስራት የነሱን የእርሻ ምርቶች ገበሬዎ ቻቸው ካመረቱበት ዋጋ በታች እኛ አገሮች እያመጡ ይሸጣሉ። በዚህ አሰራር ገበሬዎቻቸው እንዳይከስሩ ደግሞ በየአመቱ በቢልዮን የሚቆጠር ዶላር ለገበሬዎቻቸው በእርሻ ድጎማ ስም ይ ከፍላሉ። በዚህ «ደምፒንግ» ተብሎ በሚታወቀውና በነጻ ገበያ መርህዎች ክልክል በሆነ ዘዴ የ በለጸጉት አገሮች ገበሬዎች ከኛ ድሃ ገበሬዎች ጋር የሚፎካከሩበትና «እሸነፍን» የሚሉበት ሁኔ ታ ይፈጠራል። ኢትዮጵያን በተመለከተ ባለፈው ሳምንት የወጣ የተባበሩት መንግስታት ሪፖርት በሃገራችን ከሁለት አመታት ወዲህ ተከስቶ ገበሬዎቻችንን ለአስከፊ ችግር እየዳረገ ያለው የእ

ህል ዋጋ ማሽቆልቆል በቀጥታ በዚህ መልክ ከበለጸጉት አገሮች እየገባ ገበያ ላይ የሚውለውና
አልፎ ተርፎ ለርሃብ እርዳታ እየተባለ የሚገባው እህል እንደሆነ ጠቁሟል።

በእርግጥ ርሃብ ከአለም ገጽ ይጥፋ ብለው የሚታገሉ ሃይሎች «ፍትሃዊ ንግድ» ብለው ሲነ
ሱ የሚያራምዱት ጥንድ አቋዋም በአንድ በኩል የድሃ አገሮች የእርሻ ምርቶች በበለጸጉት አገ
ሮች ገባያ እንዳይደርሱ በሰበብ አስባቡ የሚጭኑትን ቀረጥ እንዲያነሱ ይጠይቃል። በሌላ በኩ
ል ደግሞ እነዚህ አገሮች ለራሳቸው ገበሬዎች በቢልየን ዶላር ድጎማ እያደረጉ ምርቶቻቸውን
በአልባሌ ዋጋ ድሆች አገሮች ገበያ እያፈሰሱ የነዚህን አገሮች ገበሬዎች ጥቅምና ህልውና መጋ
ፋት ያቁሙ የሚል አቋም ነው።

ሁለተኛውንና «የምግብ ሉአላዊነት» የሚለውን አቋም የሚያራምዱ ሃይሎች በበኩላቸው
መነሻ አድርገው የሚያራምዱት አቋም የምግብ መብት መሰረታዊ ሰብአዊ መብት እንደመሆኑ
መጠን ማንም ህዝብ ሆነ ማንም አገር ይህንን መሰረታዊ መብት ለማረጋገጥ ይስማማኛል የሚለ
ውን ማንኛውንም ፖሊሲ ያለአንዳች የውጭ ጣልቃ ገብነት ከስራ ላይ የማዋል መብቱ መረጋገ
ጥ አለበት ይላሉ። ይህንን ታዲያ ማን ይቃወመዋል?? የበለጸጉት አገሮች በአጠቃላይ፣ እንደ አ
ለም ባንክ፣ የአለም የገንዘብ ድርጅትና የአለም የንግድ ድርጅት በተለይ ይህንን አቋም በጥብቅ
ይቃወማሉ። ለምን?

ከዚህ አቋም ጀርባ ሁለት መሰረታዊ ሃሳቦች አሉ። አንደኛው ይህንን የምግብ ሉአላዊነት ለ
ማረጋገጥ የምግብ ንግድ ከአለም አቀፍ የነጻ ገበያ መርህዎች ውጭ መሆን ይገባዋል የሚልና
አንድ መንግስት የራሱን ገበሬዎች ለመጠበቅና ለመንከባከብ ወደ አገሩ በሚገባ እህል ላይ የፈ
ለገውን ያህል ታሪፍ የማድረግ መብት ይኖረዋል የሚል አቋም ነው። ሁለተኛ ደግሞ እነዚህ አ
ለም አቀፍ ተቋማትና የበለጸጉ መንግስታት « እድገት ማለት በአለም አጠቃላይ ገበያ መሳተፍ
ማለት ነው» የሚሉትን ፊሊጥ ተቃውሞ የሃገሮች እድገት በተለይም ደግሞ የርሃብ መውደም
እድል የሚረጋገጠው አንድ አገር በውጩ «ግሎባል» ወይም «አጠቃላይ» ገበያ ሳይሆን በውስ
ጥ ገበያው መዳበር ላይ ሲያተኩር ነው በማለት ይከራከራል።

እንግዲህ ለማጠቃለል። የዛሬ አርባ አመት ይወድማል ተብሎ የተዛተበት ርሃብ እስከዛሬ አ
ብሮን አለ። ከይወድማል ወደ «ይቀንሳል» ብንወርድም አሁን ባለው የአለም ሁኔታ ይህንን መ
ቅሰፍት በግማሽም በሲሶም፣ በሩብም ለመቀነስ ገና ስልሳ አመት ይህል ሊያስፈልግ ይችላል ተ
ብለናል። በዚህ የውድመት አካሄድ እስከስልሳ አመት ከጠበቅን ህዝባችንም አገራችንም ህልው
ናቸው ራሱ አደጋ ላይ የሚወድቁበት ሁኔታ ቀድሞ ይደርሳል የሚል ስጋት አለን። ይህ ከመሆ
ኑ በፊት የሃገራችን ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች በሙሉ ችግሩ የህልውናና የሞት ሽረት ጉዳይ
መሆኑን ተገንዝበን ባንድነት ግልጽ አማራጭ ይዘን ከገበሬዎቻችን፣ ከርሃብተኞቻችንና ከህዝባ
ችን ጎን መሰለፍ ግዴታችን ነው።